# <u>ቅኔ፡ ዘጥሻ !</u>

(ገሞራዉ)

(ቱጥቋጠ፣ጫካ፣ዱር … በእንግሊዝኛ ቡሽ)

የወቅቱ፡ ቅኔዬ፡ "ለጥሻ" የተመደበ፡ ነዉ፡፡ ታስታዉሱልኝ፡ እንደሆነ፡ ቀደም ሲል፣ "በነገረ-ተክል" ላይ፡ መንታ ቅኔዎች፡ አቅርቤአለሁ፡፡ "ቅኔ-ዘብርቱካን" እና "ቅኔ-ዘኮፊ (ቡና)"፡፡ ብዙዎች፡ እንደተደሰቱባቸዉ፡ ማስረጃ፡ አግኝቻለሁ፡፡ ዛሬም፡ በዚሁ፡ ነገረ-ተክል፡ ላይ፡ ጎዳናዬን፡ በማቅናት፡ "ቅኔ-ዘጥሻ"፡ የሚል፡ ግጥሜን አቅርቤአለሁ፡፡ ዛሬም፡ እንደወትሮዬ፡ ከነገረ-ተክል፡ ርዕሳዊ፣ ክልል፡ አለመዛነፌ፣ ዕፅዋት፡ ብዙኃን፡ ሊያጽፉ፡ የሚችሉ በቁዔት (በቋሚ-ነገር)፡ ያሏቸዉ፡ ተፈጥሯአዊ፡ ዘርፍ፡ በመሆናቸዉ፡ ነዉ፡፡ ርዕሱ፡ በአጠቃላይ፡ ተቋጭቶ፡ እስከተጠናቀቀም፡ ድረስ፡ ከነገረ-ተክል፡ ላለመዉጣት፡ ወስኛለሁ፡፡

ከልሒቅ፡ እስከደቂቅ፡ ሁሉም፡ እንደሚያዉቀዉ፡ ሁሉ፡ ከምድራችን፡ ላይ፡ ሠፍነዉ፡ ከሚገኙት፡ የተፈጥሮ፡ ብዙኃን፡ ክምችት፡ ዉስጥ፡ ከፍተኛዉን፡ ድርሻ፡ ይዞ፡ የሚገኘዉ፡ የዕፅዋት፡ ዓይነትና፡ የተንቀሳቃሽ፡ ፍጡራን፡ ጓዝና፡ ክምችት፡ ነዉ፡፡ ፈረንጁ፡ "Plant and Animal Kingdom" በማለት: በሁለት፡ ዘርፈ፡ መንግሥት፡ ይመድባቸዋል፡፡ Biology, Botany …ወዘተ፡ እያለ፡ በመከፋፈል፡ ዝርዝር፡ ጥናት፡ አርጎባቸዋል፡፡ ቢዝቁት፡ የማያልቅ፡ ተፈጥሯአዊ፡ ዕዉቀት፡ የተከማቸበት፡ የጥናት፡ መስክ፡ ነዉ፡፡ ከሥሩቱና፡ ከጥልቀቱ፡ የተነሣ፡ እንደ፡ ባሕረ-ሀሳብ፡ ናላ፡ ያዞራል፡፡ ቅርንጫፉ፡ ብቻ፡ እልቁ መሣፍርት፡የለዉም፡፡ በነገረ-እንስሳቱ፡ ዉስጥ፡ ብቻ፡ ከሚጢጢቱ፣ ሐይድራ (ባለ፡ አንድ፡ ሴል፡ ፍጡር)፡ አንስቶ፡ እስከ፡ ግዙፍ፡ ዳይናሦር፡ ድረስ፡ ያለዉ፡ የፍጡራን፡ ዝርያ፡ ብቻ፡ በዝርዝር፡ እናጥናህ፡ ቢሉት፣ ቆበር፡ ያስደፍቃል፡፡ በዚህ፡ ሰፊ፡ የጥናት፡ መስክ፡ ላይ፡ ለተሠማሩት፡ ወገኖች፡ ሊቃዉንት፡ አፅናይ፡ መጽኔዉን፡ ይስጣቸዉ፣ እንጂ፣ ያመቀዉ፡ ጥበብና፡ ዕዉቀት፡ ዝቀዉ፡ የሚጨርሱት፡ አይደለም፡ እንደኔ፡ ያለዉ፣ ኩታራ፡ ብዕረኛ፡ ግን፡ ከእፍታዉና፡ ከገፈቱ፡ ላይ፣ ትንሽ፡ ትንሽ፡ እየጨለፈ፣ ለአንባቢያን፡ ማቅረቡን፡ መርጧል፡፡ በጥቂቱ፡ ብቻ፡ መቅረቡ፣ የአንባቢያኑን፡ ጊዜ፡ ለመቆጠብና፣ ጉልበታቸዉንም፡ ለማካበት፡ ብዬ፡ የዘየድኩት፡ መላ፡ ነዉ፡፡ ስለዚህም፡ ነዉ፣ አንዴ፡ "ቅኔ-ዘብርቱካን"፣ ሌላ፡ ጊዜ፡ ደግሞ፡ "ቅኔ-ዘቡና" እያልኩ፡ እየሸራረፍኩ፡ የማቀርበዉ፡፡ የቅኔዎቹ፡ አንባቢዎች፡ እዚህና፡ እዚያ፡ መርገጤን፣ ታዝበዉ፡ ትዕግሥታቸዉን፡ እንደማይነፍጉኝ፡ ተስፋ፡ አደርጋለሁ፡፡ ለታላላቅ፡ እንደ፡ ኖቭል (ጠብደል፡ ልብ፣ ወለድ)፣ ላሉ፡ መጻህፍቶቼ፡ የተጠቀምኩባዉ፡ ከፍተኛ፡ የተክል፣ ዓይነቶች፣ በምድረ-ኢትዮጵያ፡ ዉስጥ፡ ይገኛሉ፡፡ እንደ "ዕንጎችት" (ዕፀ-ኢየሱስ)፣ እንደ፡ ዕፀ-ኮሞል፣ እንደ፡ "ዕፀ-ዘዌ"… የመሳሰሉት፡ ናቸዉ፡፡ አንደኛዉ፡ ዕፅ፣ የሰዉን፡ ልጅ፡ ከነአካላዊ፡ ግዝፈቱ፡ መሠወር፡ የሚችል፡ ሲሆን፡ ሌላዉ፡ ደግሞ፣ ደደቡንና፡ ደንቆሮዉን፡ የሰዉ፡ ልጅ፡ ከነደደብነቱና፡ ከነድንቁርናዉ፡ መንጥቆ፡ ነፃ፡ የሚያወጣዉ፡ ነዉ፡፡ እንደዚያ፡ ያሉ ዕፅዋት፣ ሁሉ፣ ብታምኑም፡ ባታምኑም፣ በሀገራችን፡ ኢትዮጵያ፡ ምድር፡ ላይ፡ በቅለዉ፡ ይገኛሉ፡፡

ለምሣሌ፣ ከጣና፡ሐይቅ፡ ዉስጥ፣ በምትገኝ፡ አንዲት፡ ደሴት፣ ላይ - "ደሴት-ናግራን" - ይሏታል፣ አንዲት፡ ልዩ፡ ተክል፡ አለች፡፡ የቅጠሎቿን፡ ልምላሜና፣ የቅርንጫፎቹን" ሐረጋዊ፡ አዘነባጠፍ (አወራረድ)፡ ልብ ብሎ፡ ለተመለከተዉ፣ ከሚታሰበዉ፡ በላይ፣ እጅግ፡ ታምራለች፡፡ ይህችም፡ ዕፅ: ባላት፡ ልዩ፡ ተፈጥሯአዊ፡ ፀጋና፡ ልግሥና፡ የተነሣ፣ ልዩ፣ የሆነ፡ አንድ፡ አሥደናቂ፣ ትንግርት፡ ትፈፅማለች፡፡ ይኸዉም፡ አንድ፡ ብሶት፡ ያጨናበሰዉ፡ ካንጀቱ፡ ሀዘን፡ ተሰምቶት፡ ከዚች፡ ተክል፡

ጥላ፡ ሥር፡ ሄዶ፡ ከግርጌዋ፡ ስር፡ ቢቀመጥ፤ ተክሊቱ፡ ከአዘነዉ ሰዉ፡ ብሶት፡ ለማፅናናት፡ ይመስላል፤ ቅጠሎቿን፡ በሙሉ፤ በፀፀት፡ ታረግፍለታለች፡፡ ይህን፡ ትንግርት፡ የትኛዉም፡ ወገን፤ በበጋዉ፡ ወቅት፡ ከቦታዉ፡ በመገኘት፡ በግሉ፡ ማየት፡ ይችላል፡፡

እንደ ባሕላዉያኑ፡ የሀገራችን፤ ምሁራንና፡ ሊቃዉንት፡ ጥናት፡ ከሆነ፣ ነገደ-ዕፅዋት፡ በሁለት፡ ዐበይት፡ ክፍላት፡ ይመደባሉ፡፡ "ዕፅ-ዘየሐድ" (ሕይወት-ነሽ - ወይም፡ "መጋብያነ-ሕይወት") እና. "ዕፅ-ዘይቀትል" (ሕይወት-ነሽ - ወይም፤ መቅትለ-ህይወት) ይሏቸዋል፡፡ እንደባሕርያቸዉም፡ሁኔታ፤ አንፃራዊ፡ አገልግሎት፡ አላቸዉ፡፡ ተንኮለኛ፡ ደብተራ፡ ከወደጓሮዉ፡ ብቅ፡ ብሎ፤ ቆርጦ፡ የሚያመጣት፡ ቅንጣት፡ ቅጠል፡ የትልቅ፡ ሰዉ፡ ነፍስ፡ ለማጥፋት፡ ፍፁማዊ፡ የሆነ፡ ጉልበትና፡ ልዩ፡ ኃይል (መርዝነት) አላት፡፡ የሁለተኛዉ፡ ምድብ፡ ዓይነት፡ ተክል፡ መሆኗ፡ ነዉ፡፡ በዚያዉ፡ አንፃር፡ ደግሞ፡ ከመንገድ፤ ዳር፡ በቅላ፡ ከምትገኝ፡ እዚህ፡ ግቢ፡ ከማይሏት፡ የተክል፡ ዘለላ፤ ላይ፡ ያለችን፡ ቅጠል፤ ትንሽ፡ ቀንጠብ፤ አርጎ፤ ማንም፡ አይንካኝ፡ ብላ፡ በትምክህትና፡ በኩራት፡ ከምትወጣጠር፡ ሴት፡ ወይዘሮ (ዉብና፡ ቆንጆ፡ የሆነች) ትኩስ፡ ሽንት፡ ላይ፤ ጣል፤ ሲያደርገዉ፤ ከልኩ፡ ባለፈ፤ ቅንዘራ፡ አብዳ፤ ካላንደፋደፍ ይመስለኛል፡፡ የሚቀረኝ፡ ነጥብ፡ ቢኖር፡ "ጥሻ"፡ የምንለዉ፤ የተክሎች፡ ቁጥቋጦ፤ የሚሰጠዉ፡ ልዩ፡ ጠቀሜታ፡ ለምን፡ እንደሆነ፡ መግለጹ፡ ብቻ፡ ነዉ፡፡ በነገራችን፡ ላይ፤ በፈረንጅኛዉ፡ ቋንቋዊ፡ ይትብሃል፤ ጥሻ፡ ለሚለዉ፡ ተመጣጣኝ፡ ትርጉም፤ በልሳነ፡ እግልጣር፤ "Bush' የሚለዉ፡ ቃል፡ እንደሆነ፤ አንባቢዎቼ፡ በሙሉ፡ የምታዉቁልኝ፡ ይመስለኛል፡፡ የቡሽ፡ ተክላዊ፡ ተፈጥሮ፤ ሆነ፡ ተብሎ፡ ለእንስሳትና፡ በተለይም፡- ለአራዊት፡ እንደልዩ፡ መደበቂያ፡ መነኻርያ፡ የተፈጠረ፡ ይመስላል፡፡ ብዙዉን፡ ጊዜ፡ ገለልተኛ፡ የሆነ፡ መካን (ቦታ) ፈልጎ፡ "ቡፍ" እና፤ "ጅብ" ብሎ፡ ይበቅላል፡፡ በሦስቱም፡ ክፍላተ- መልክዐ-ምድር፡ ላይ፡ ይገኛል፡፡ በደጋ፤ በቆላና- በወይናደጋ፡፡ ለየት፤ባለ- ባሕርይም፤ ጭዉ፡ ካለ-በረሀ፡ ዉስጥም፣አልፎ፤ አልፎ፡ ይገኛል፡፡ አብዛኛዉን፡ ጊዜ፤ በነባር፡ አገልግሎቱ፤ የሚታወቀዉ፤ ብዙኃን- አራዊትና፤ እንሰሳትን፡ በጉያዉ፤ ይዞ፡ ማስተነናገዱ፤ ነዉ፡፡ እንደየቦታዉ፡ ባሕርይ፤ ጥንቸሎች፤ ሰሶች፤ አጋዘኖች፤ የሜዳ-አህዮችና ነብሮች፤ አንበሶች፤ ቀበሮዎች፤ ተኩላዎች፤ ጅቦች - የመሳሰሉትም፡ ሁሉ፡፡ በጥሻ፡ ዉስጥ፡ የሚገኙ፡ ዕፅዋት- በአፈጣጠራቸዉ፡ ረገድ፤ አዉቆ-በቀሎች፡ ናቸዉ፡፡

እንደተቀሩት፡ ተክሎች፡ ሰዉ፡ አይተክላቸዉም፡፡ ሾም ሾም፡ ብለዉ፡ በመጠጋጋት፡ የበቀሉ፡ በመሆናዉ፡ እንደግል፡ መኖሪያቸዉ፡ አርገዉ፡ የሚጠበቁበት፡ እንሰሳትና፡ አራዊት፤ የፀጥታና፡ የሰላም (security) ሥፍነት፡ የተጠበቀበትና፡ ፍጹም፡ ዋስትና፡ የሚሰጥ፡ መሆኑን፡ ይተማመኑበታል፡፡ ችም፡ ችም፡ ያ ፡ በመሆኑም፡ ለብርድና፡ ለቆራ፡ ስለማያጋልጥ፤ ሙቀቱ፡ እጅግ፡ ያዝናናቸዋል፡፡ በመሆኑም፤ ምድረ-አራዊት፡ ፡ ተመሳሳይ፡ ዘሩን፡ በገፍ፡ እየፈለፈለ፡ ይራባበታል፡፡ ከዚያ፡ በኋላ፡ ነዉ፡ የፈለፈላቸዉ፡ እምቦሶች፡ ሲጎለብቱ፡ ከጥሻ፡ ቤታቸዉ፡ በመዉጣት፡ በየከተማዉ"ለዘሁሉ" የሚሠማሩት፡ ዋናዉ፡ አለኝታቸዉና፡ ትምህክታቸዉ፡ ግን፤ ምንጊዜም፡ "ጥሻ" ነዉ፡፡ ይህ፡ ልዩ፡ የጥሻ፡ ኩነታዊ፡ በሕርይ፡ ነዉ፡ ይህን፡ቅኔ፡ እንዲበርቅና፡ በአደበባይም፡ እንዲሠራጭ፡ ያደረገዉ፡፡ እኔም፡ የጥሻን፡ ባሕርያዊ፡ ሁኔታ፡ ከቅኔ፡ ሥልታዊ፡ ድንጋጌ፡ ጋር፡ በማዋሐድ፡ የሰዎችን፡ ዉስጣዊ፡ ስሜት፡ በሚነካና፡ በሚገጭ፡ መልኩ፡ ቡጡን፡ ፈልፍዬ፡ በማዉጣት፤ እንደ፡ ሕሊና፡ ጣፋጭ፡ ማዕድ፡ በማዘጋጀት፡ ይህን፡ ቅኔ፡ ያቀረብኩት፡፡ አንባብያን፡ በሙሉ፡ እንደምትዝናኑበትና፡ እንደምትደሰቱበት፡ ተስፋ፡ አደርጋለሁ፡፡

## ቅኔ-ዘጥሻ

በዉስጡ፡ አጭቆ - የዕፅዋት፡ ዓይነት፣
ችምችም፡ በማለቱ - በተፈጥሮዉ፡ ሥሬት፣
እጅግ፡ ይወዱታል - እንስሳት፡ አራዊት፡፡
ስለዚህኮ፡ ነዉ - በዚያ፡ መኖራቸዉ፣
አራዊት፡ በሙሉ - ስለተስመማማቸዉ፣
እንዲያ፡ የሚዝናኑት - "ጥሻን"፡ ወገን፡ አርገዉ፣

* * * O * * *




የሚዘርፉትን፡ ከብት - ሌሎችንም፡ ሀብታት፣
ከከተማ፡ ወስደዉ - በጥሻ፡ እሚያኖሩት፣
የሰዉ፡ ልጅ፡ ጠላቶች - ጠቅላ ዉ፡ አራዊት፡፡
ተማምነዉበት፡ ነዉ - ጥሻቸዉን፡ ከልብ፣
ዋስትና፡ ስላለዉ - አዝናኝ፡ ያለ፡ ሐሳብ፣
ሽፋን፡ በመስጠቱ - መለስ፡ ቀለስ፡ ሲሉ፡ ለዘረፋዉ፡ ጥበብ፣

* * * O * * *

ጨካኝ፡ አዉሬ፡ - ንጹሐንን፡ ገድሎ፣
ሊደበቅ፡ ይገባል - ከጥሻ፡ ዉስጥ፡ ዘሎ፡፡
ይህንንም፡ ሲያደርግ - ለዓመታት፡ ኖሯል፣
ለመንጎች፡ አራዊት - ከለላነት፡ ሰጥቷል፡፡

* * * O * * *

ያዉሬ፡ መናኸሪያዉ - ጥሻዉ፡ ቤተ - መንግሥት፣
ስንቶችን፡ ፈልፍሎ - ባለም፡ በያለበት፣
ሽብር፡ እያስነሳ - ነፍጎና፡ ነፃነት፡፡
የቆርኪ፡ የቡሹ - የጠርሙስ፡ መክደኛዉ፣
አብዛኛዉን፡ ጊዜ - የሚፈበረከዉ፣
ያራዊት፡ መኖሪያ - መሥሪያዉ፡ ቤት፡ ከሆነዉ፣
ጫካና ቁጥቋጦ - ብለን፡ ከምንጠራዉ፣
መገኛና፡ ምንጩ - ጥሻ፡ ነዉ፡ ፈብሪካዉ፡፡

* * * O * * *

ወላ፡ የቡሽ፡ ዓይነት - ሥሪቱ፡ ፍጥረቱ፣
ለማፈን፡ ለማመቅ - ሆኖ፡ መሠረቱ፣
እንዳስጨነቀ፡ አለ - ባለም፡ እየዞረ፣
እጅግ፣አስመርሮ - ሕዝብ፡ እየዘረረ፡፡

*    *    *    O    *    *    *

ይኼን፡ አስመልክቼ - እኔም፡ ከዚህ ቀደም፣
ተቀኝቼ፡ ነበር - ቅኔ፡ የሚያስደምም፣
‹‹ አለቅጥ፡ ቢጠማኝ - መጠጥ፡ አስፈልጎኝ፣
ከፍቼ ልጠጣ - ጠርሙስ፡ ጠጅ፡ አጋጥሞኝ፣
በኃይል፡ ተቀርቅሮ - ያ፡ ቡሽ፡ አስቸገረኝ፡፡››

*   *   *    O    *   *   *

መንነዉ፡ የወጡ - ሰዎች፡ ከከተማ፣
ናዝራዉያን፡ ሆኑ - ግሑስ፡ ሰዉ፡ ደካማ፣
ሔድዉ፡ የሚገቡት - ማረፊያ፡ ቤታቸዉ፣
ጥሻ፡ እንደሆነ - ታዉቋል፡ መድረሻቸዉ፡፡
ቤታቸዉ፡ መሆኑ - በጭራሽ፡ ባልከፋ፣
አረሙና፡ አጋሙ - መርዘኛዉ፡ አንተርፋ፣
በጥሻ፡ ዉስጥ፡ ያለዉ - አድጎ እየፋፋ፣
እያሠቃያቸዉ - ካልቆረጡ፡ ተስፋ፡፡

*   *   *    O    *   *    *

ለምን ይቃዣሉ - ሰዎች፡ በጎ፡ ነገር፣
ጥሻ፡ ዉስጥ፡ እስካሉ - ሲታወቅ፡ እንዳይኖር፣
ሰላምና፡ ሕይወት - በምንም፤ ተዓምር፡፡
ካዉሬ፡ ተጎራብቶ - ምን፡ ሰላም፡ ይኖራል፣
በጣም፡ የራበዉ፡ ለት - ለአፉኪ፡ ይላል፣
ጠኔ፡ ሲያጣድፈዉ - አይምርም፤ ይዉጣል፡፡
ጥሻ፡ እስካሉ፡ ድረስ - ሰዎች፡በዚህ፡ ዓለም፣
መታፈን፡ ያለ፡ ነዉ - ምኔም፡ ለዘላላም፣
ችምችም፡ ያለዉ፡ ጫካ - ስለማይፈጥር፡ ሰላም፡፡
መተንፈሻ፡ ሳይኖር -የማያነቃንቅ፣
የጥሻ፡ ሥረዓት፡ ነዉ - አፈኖ፡ ማስጨነቅ፡፡

*   *   *    O    *   *   *

ገዳይ፡ ይዘልና - ከጥሻዉ፡ ይገባል፣
እሱ፡ እንዲጠብቀዉ - በከለላዉ ያምናል፡፡
የኋላ፡ ኋላ፡ ግን - ሠደድ፡ ተነስቶበት፣
ሊቃጠል፡ ቢጠፋ- ተክሉ፡ ሲጋይበት፣
የት፡ ይሆን፡ መድረሻዉ - አዉሬዉ፡ የሰዉ ፍኻርት?

*   *   *    O    *   *   *

የአዉሬነት፡ ጠባይ - ያለዉ፡ አንዳንድ፡ ሰዉ፣
ጥሻን፡ ይመኘዋል - በመሸፈን፡ ሙያዉ፡፡
ባያዉቀዉ፡ ነዉ፡ እንጂ - እንዳለዉ፡ አጥፊ፤ ፀር፣
ድምጥማጡን፡ ሠራዥ - እሳት፡ ቀመስ፡ ዓየር፡፡

ሠደድ፡ የሚባለዉ - ከነስሙ፡ ጭምር!!

* * * O * * *

አዉሬ፡ እያረባ - ካስቸገረ፡ ጥሻ፣
ሰዎች፡ እየጠፉ - ካሳጣ፡ መድረሻ፣
አማራጭ፡ የለዉም - ለጥሻ፡ በምድር፣
ከመመንጠርና - ከማቃጠል፡ በቀር፡፡

* * * O * * *

አዲስ፡ በቀል፡ ሕይወት - ለምልሞ፡ እንዲኖር፣
ያዉሬዎችን፡ ጥሻ - የንፁሐንን፡ ፀር፣
ሕጉ፡ የግድ፡ ይላል - ያን፡ ጥሻ፡ መመንጠር፡፡

* * * O * * *

የጥበብ፡ እንጂ፡ ነዉ - የጉልበት፡ አይደለም፣
አሮጌዉን፡ ጥሻ - አቃጥሎ፡ ማለምለም፣

* * * O * * *

ዳር፡ ዳር፡ እያለ፡ ነዉ - የቃጠሎዉ፡ ምጣት፣
ለብልቦ፡ ሊያጠፋዉ - ባልጠበቀዉ፡ ስዓት፡፡
እስከዚያዉ፡ ድረስ፡ ግን - ስንቶች፡ ተሠቃዩ፣
ከጥሻዉ፡ ከፊሉት - አዉሬዎች፤ ሲጋዩ፡፡

* * * O * * *

ምድረ አንበጣና ጠቅላለዉም ፊንጣ፣
እየፈለፈለ ጥሻዉ እያወጣ፣
ስንቱን፤ አስጨረሰ - ንፁሐን፡ ወገኖች፣
ከቤታቸዉ፡ ገብ - ፍፁም፡ መስሎ፡ ዛሮች፡፡

* * * O * * *

ተፈልፍሎ፡ አድጎ - በየጥሻዉ፡ ገጠር፣
ጭከናን-ተምሮ - ሠይጥኖ፡ ባላጋር፣
በስተመጨረሻዉ - ይዘምታል፡ ከተማ፣
ሰዉን፡ ለረፈርፍ - በያዘዉ፡ ዓላማ፡፡

* * * O * * *

አዶከብሬዉ፡ ዛሩ - ጋኔል፡ ሌጌዎኑ፣
የመናፍስት፡ ዘር - ጠቅላላዉ፡ ሠይጣኑ፣
ሌሊት፡ በጭለማ - የሚያድረዉ ሲያጠቃ፣
በመንፈቀ፡ ሌሊት - በጠፉ፡ ጨረቃ፣

ኀሐ-ጽባሕ፡ ቀዶ - ብርሃ፡ ሲፈነጥቅ፣
የፀዳል፡ ፀሓይ - ብርሃን፡ ሲፍለቀለቅ፣
ተንደርድሮ፣ ሔዶ - መደበቂያዉ፡ ዋሻ፣
እንደሆነ፡ ታዉቋል - ገጠሩ፡ ጥሻ፣
የሚያጠፋዉ፡ ፀሩ - ቀጥቃጩ፡ መዶሻ፣
ወልደ-ፀሐይ፡ ብርሃ - ነዉና፡ ማፍረሻ፣
ለንፁሐን፡ ሰዎች - ተከላካይ፡ ጋሻ፡፡

*   *   *      O      *   *   *

ፀሐይ፡ ብቅ፡ ሰትል ግለትን፡ ተላብሳ፣
ከሁሉ፡ አስቀድሞ - ለነፍሱ፡ እንደሚሳሳ፣
ራሱ፡ ጥሻ፡ ነዉ - ለመዳን ካበሳ፣
እግሬ-አዉጭኝ፡ ብሎ - የሚከንፍ፡ በሃምሣ፣
ሲነድ፡     መሆን - አመዱን፡ ሬሣ!!

*   *   *      O      *   *   *

ምነዉ፡ የዘመኑ - ያ፡ ጥሻ፡ ጨከነ፣
አራዊት፡ አርብቶ - ሕዝብ፡ ላይ፡ በተነ፡፡

*   *   *      O      *   *   *

ስንቱን፡ እሚጨርስ - ከተማ፡ እየላከ፣
የገጠሩ፡ ጥሻ - አዉሬን፡ ያመለከ፣
ከተክሎች፡ ዝርያ - ለክሦ ያወከ፣
ከተፈጥሮዉ፡ ስቶ - ነፍሳትን፡ ያኘከ!!

*   *   *      O      *   *   *

የጊዜ፡ ጉዳይ፡ ነዉ - ፍርድማ፡ ይኖራል፣
ሲገድል፡ እንደኖረዉ - እሱም፡ ይቃጠላል፣
በረድ፡ ወይም፡ ሠደድ - ያኮማትረዋል፣
አዉሬዉ ሲያገባ - አይከርምም፡ ይሞታል፡፡

*   *   *      O      *   *   *

በሾክ፡ አሜከላ - ደጁ፡ ኀሮዉ፡ ታጥሮ፣
አይኖርም፡ ሁልጊዜ ተፈርቶ፡ ተከብሮ፣
ይጠፋታል፡ እንጅ - አንድ ቀን፡ ተወሮ፣
በሰደድ፡ ሠራዊት  ጥሻ፡ ተኮማትሮ፡፡

*   *   *      O      *   *   *

ከሕግ፡ የተጣላ - አማፅያን፡ ሁሉ፣
መሸሸጊያ፡ አርኀታል - ለወንጀሉ፡ ሁሉ፣
የስንቱን፡ ንፁሕ፡ ደም - ያፈሰሰ፡ ገዳይ፣

መደበቂያ፡ ዋሻዉ - ጥሻ፡ አይደለም፡ ወይ?
ከቶ፡ በምድር፡ ላይ - ፍፁም፡ ወንጀለኛ፣
የታል: እንደጥሻ - የሕይወት፡ ቀበኛ?
ለገዳዮች፡ - የሚሰጥ፡ ከለላ፣
ባለም፡ ላይ፡ የታለ - እንደጥሻ፡ ?
አዉሬዎች፡ አርብቶ - ከተማ፡ የሚልክ፣
የታል፡ እንደጥሻ - የረገመዉ፡ አምላክ?
ስንቱ፡ ነዉ፡ ተናግሮ - መጨረስ፡ ይቻላል?
ጥሻ፡ ያሳየዉን - መከራና፡ ተንኮል!
እንደትሻነቱ - ድርብ፡ ደባ፡ ሰርቷል፣
በየዋህ፡ ህዝብ፡ ላይ - ፀያፍ፡ ቅርሻት፡ ተፍቷል፡፡

* * * O * * *

ትንታግ፡ ታህል፡ ትንኝ - በጫረችዉ፡ ዕለት፣
ግዙፉን፡ ዳናሦር - አንጋፎች፡ የፍጥረት፣
በቅፅበት፡ ጠፍተዋል - ሳያስቡት፡ ድንገት፣
የጥሻም፡ ፍፃሜ - እንዲሁ፡ ይሆናል፣
ባልጠበቀዉ፡ ጊዜ - ዶጋመድ፡ ይበላል፡፡

* * * O * * *

እስከዚያዉ፡ ጊዜ፡ ግን - ገድሎ ይተረካል፣
የጥሻ፡ ምንነት - ሠንኮፉም፡ ይነካል፣
አከርካሪዉ፡ ሳይቀር - አንድ፡ ባንድ፡ ይደቃል፡፡

* * * O * * *

ይበልጥም፡ ማተኮር - ያለብን፡ በትችት፣
በወንጀሎች፡ ነዉ - በነሳዉ፡ ነፃነት፣
በፍትሕና፡ በሃቅ - እንዲያም፡ ሲል፡ በሰዉ፡ መብት፣
ሲያላግጥ፡ በኖረዉ - በዎገኖች፡ ሕይወት፡፡
የቡሽ፡ ወንጀልማ - ስንቱ፡ ይነገራል?
በዉስጡ፡ ያሉትን - አራዊትና፡ ተክል?
በመርዙ፡ በክሎ- ዱሩ፡ በሚያመርተዉ፣
የሰዉን፡ ኅሊና - ፉዞ፡ በሚያደርገዉ፣
በዕፀ-ፋርሱ፡ ሆነ- ባሲዳም፡ አብሾዉ፣
እየጋተ - ከልጅ፡ እስካዋቂዉ፣
ስንቱን፡አድርጎታል - ቀልበ ቢስ፡ ዕብድ፡ሰዉ፡፡

* * * O * * *

በመርዛም፡ ተክሉ - ሰዉ፡ እያሳበደ፣
ከተማ፡ በመላክ - እያወናበደ፣
ስንቱን፡ ንፁሐን፡ ሰዉ - በእምርክክ፡ አስሄደ?
ከቤቱ፡ ከቀዬዉ - ገብቶ፡ እያሳደደ!!

* * * O * * *

የመርዙ፡ማዕጠንት - ራሱ፡ ሲሸተዉ፣
ጠረኑና፡ ሽታዉ - መንፈሱን፡ ሲያዉደዉ፣
ያ፡ ቡሽ፡ አይደለም፡ ወይ? ሰዉ፡ ጤና፡ የነሣዉ፡፡

*  *  *  O  *  *  *

እንዴት፡ ትላላችሁ? - ይህ፡ ዓይነቱ፡ በደል፣
በነፍስ፡ አያስቀጣ - አያስፈርድ፡ ባካል፣
በሰዉ፡ ልጅ፡ ሲጫወት - ተራዉ-አረም-በቀል፣
እሾህ፡ አሜከላዉ - አጋሙ፡ በጥቅል!!

*  *  *  O  *  *  *

አያ፡ ጥሻ፡ ሆዬ - የአረሞች፡ ዕምቅ፣
ከዚህ፡ ከዚያ፡ ብሎ - ስቦ፡ ባመጣዉ፡ ጠንቅ፣
ዳፋዉ፡ እያረገ - አጉል፡ ሲመፃደቅ፣
በዉስጡ፡ ያሉትን - ነፍስ፡ ያለዉን፡ ደቂቅ፣
በወረደዉ፡ አሲድ - ሠደዳዊ፡ መብረቅ፣
ስንቱ፡ ፍጡር፡ አልቋል - ምንም፡ነገር፡ ሳያዉቅ!!

*  *  *  O  *  *  *

ዱሩ፡ ቤቴ፡ ብሎ - ይኖር፡ የነበረዉ፣
በጥሻዉ፡ ተማምኖ - ተጠግቶ፡ ያለዉ፣
ትንሹ፡ ትልቁ - ወጣት፡ ሽማግሌዉ፣
ስንቱ፡ ተቃጠለ - በተነሣዉ፡ ዕሳት፣
መቱን፡ እየጋየ - ተፈጀ፡ ባንድነት!
ባልጠበቀዉ፡ ጊዜ - ባልጠበቀዉ፡ ሰዓት፡፡
በሚያመርተዉ፡ ፍዳ - በሚፈትለዉ፡ በደል፣
ስንቱን፡ አድርጎታል - እብድ፡ሰዉ፡ ነሆለል!

*  *  *  O  *  *  *

በሚሠራዉ፡ ደርጊት - ስንቱን፡ አስመረረ፣
አዉሬ፡ እያረባ - ጥሻ፡ አስቸገረ፡፡
ከተማ፡ አስገብቶ - ሴት፡ ወንዱን፡ ዘረረ፡፡

ኧረ፡ ስንቱ፡ ስንቱ - ስንቱ፡ ይነገራል?
በጥሻ፡ የተነሣ - ስንት፡ ጉድ፡ ተሠርቷል!
ያለቀዉን፡ ቁጥር - ማን፡ ማስላት፡ ይችላል?
ዉስጡ፡ የነበረች - አንዲት፡ የሰስ፡ እናት፣
ገና፡ አራስ፡ ሆና - እርጥቧን፡ እመጫት፣
ከጨቅላ፡ ልጇ፡ ጋር - ያለች፡ ስትጫወት፣
ተቃጥላ፡ ነዳለች - ባልሰራችዉ፡ ኃጢአት፣
ያ፡ ጥሻ፡ ባመጣዉ - ታላቅ፡ የሳት፡ መቅሰፍት፣
መዘዙ፡ ኮድኩዶ - በፈጠረዉ፡ ጉዳት፡፡

* * * O * * *

ቀበሮና፡ ተኩላዉ - ጅቡናዉ፡ እርያዉ፣
ሌላዉም፡ ጀዉሳ- በልቶ፡ የማይጠግበዉ፣
በአዉሬነቱ፡ ግፍ - ነበልባል፡ ቢያጋየዉ፣
ማንም፡ አያዝንለት - ቋያ፡ ቢያቃጥለዉ፣
ለግብሩ፡ ነዉና - ተመጣጣኝ፡ ዋጋዉ፡፡
ንፁህኑ፡ እንጂ - አንጀት፡ የሚበሉት፣
ከአሉበት፡ ሰርቆ - ድንገት፡ ሲያጭዳቸዉ፡ ሞት፣
ጥሻ፡ ባመጣዉ፡ ጦስ - ሲፋቁ፡ ከሕይወት፡፡

* * * O * * *

አያድርስ፡ እንጅ፡ ነዉ - ጥሻ፡ ወለድ፡ አዉሬ፣
አንደዬ፡ ከነከሰ - ነዉና፡ አይምሬ!
ጥሻ፡ አስቸገረ - ክፋት፡ እያመቀ፣
አዉሬዎች፡ ፈልፍሎ - ስንቱን፡ አስጨነቀ፣
ወጣት፡ ሽሜ፡ ሳይል - ብዙ፡ አማቀቀ፡፡
ጥሻ፡ እየላከ - አረመኔ፡ ገዳይ፣
በስንቱ፡ አሾፈ - በዉድ፡ ሕይወት፡ ላይ፣
ልዩ፡ ፍዳና፡ ግፍ - አስገድዶ፡ ሲያሳይ፣
እየጨፈጨፈ - ወንድና፡ ሴት፡ ሳይለይ!!

* * * O * * *

ተዘርዝሮ አያልቅም - ጥሻ፡ የሠራዉ፡ ግፍ፣
ገምድዬ፡ ልተወዉ - ባጭሩ፡ ይታለፍ፣
ተደፍኖ፡ ይንተክተክ - ዘር፡ ንዘሩ፡ እስኪረግፍ!

* * * O * * *

እንግዲህ፡ ወገኖች - በየትም፡ ያላችሁ፣
ተሰባሰቡና - ባንድነት፡ ሆናችሁ፣
ጥቃቱን፡ መክቱ - ባዶናይ፡ ብላችሁ፡፡

ከብዙዎች፡ ክብሪት - አንዲት፡ ኩስታሪ፣
በቂዉ፡ ናት፡ ለጥሻ - ከፋፍላ፡ መታሪ፣
አመዱን፡ አምርታ - እርቃኑን፡ አስቀሪ፡፡
ጥሻን፡ ለመጋተር - ልብ፡ እንግዛ፡ እንግዲህ፣
ንፁሐን፡ ስብስቦ - ሳይጨርስ፡ በእልህ፣
ተነሡ፡ እንታገል - እንበለዉ፡ ይብቃህ!!